
# አዲስ አበባ
## የመዳኛችን መጀመሪያ ወይስ የመጥፊያችን መጨረሻ?




ልደቱ አያሌው
መጋቢት 21 ቀን 2016 ዓ.ም

# አዲስ አበባ
# የመዳኛችን መጀመሪያ ወይስ
# የመጥፊያችን መጨረሻ?

ይህ አጭር መጣጥፍ አዲስ ጽሁፍ አይደለም። **"የባልበላውም ጭሬ ልበትነው ፖለቲካ"** በሚል ርዕስ ከዓመት በፊት ፅፌ ካሰራጨሁት መጣጥፍ የመደምደሚያ ክፍል የተወሰደ ነው። ጽሁፉ ከተጻፈ ከዓመት በላይ ቢሆነውም ከሰሞኑ የመህል አዲስ አበባን የማፍረስ ዘመቻና ከአቶ ሽመልስ አብዲሳ የእብሪትና የዘረኝነት ንግግር ጋር በተያያዘ የአዲስ አበባ የወደፊት ዕጣ-ፈንታ ጉዳይ የበለጠ አነጋጋሪ ሆኖ ብቅ ስላለ ጽሁፉን በአስታዋሽነት እንደገና ማስነበብ ተገቢ ሆኖ አገኘሁት።

ስለሆነም ከጊዜው ጋር እንዲጣጣም ለማድረግ የሚያስችል ማሻሻያ በማድረግ የጽሁፉን **"የመደምደሚያ"** ክፍል ብቻ እንደገና እንደሚከተለው አቅርቤዋለሁ። በዚህ አጋጣሚም በአዲስ አበባ ዙሪያ ያለው ችግር ምን ያህል ፍትሀዊነት የሌለው፣ አሳሳቢና ከአጠቃላይ አገራዊ ህልውናችን ጋር የተያያዘ እንደሆነ የበለጠ ለመረዳት **"የባልበላውም ጭሬ ልበትነው ፖለቲካ"** የሚለውን መጣጥፌን አንባብያን እንደገና መለስ ብላችሁ እንድታነቡት በአክብሮት እጋብዛለሁ።

## "የባልበላውም ጭሬ ልበትነው ፖለቲካ"...
## ...መደምደሚያ

በአዲስ አበባ አስተዳደር ውስጥ የሚኖረው ህዝብና ዜጋ ከሌላው የአገሪቱ ህዝብ በተለየ በርካታ ፖለቲካዊ መብቶቹን በአገሪቱ ህገ-መንግስት ተነጥቋል። ይህ መሆኑም አላንስ ብሎ በ27 ዓመቱ የኢህአዴግ ዘመን ለበርካታ ህገ-ወጥ ተፅዕኖዎች ተጋላጭ ሆኖ ኖሯል። ይባሱኑ በአሁኑ የብልፅግና የአገዛዝ ዘመን ሁለንተናዊ ህልውናው ከፍተኛ አደጋ ላይ ወድቋል። አደጋውን በዋናነት የፈጠረውም "አዲስ አበባ የብቻዬ ናት" የሚለው የአክራሪ ብሄርተኝነት ጥያቄ ነው።

ከአራቱም የአገሪቱ ማዕዘናት የመጣ ህዝብ ከ140 በላይ ለሆኑ ዓመታት ላቡንና ጥሪቱን አፍስሶ በጋራ የገነባትን፣ ከአምስት በላይ የሆኑ ተከታታይ ትውልዶች በአንድ ላይ ከትመው የኖሩባትን፣ የሚሊዮኖች "አገር" የሆነችውንና ከኢትዮጵያ መዲናነትም አልፋ የአፍሪካ ህብረት መቀመጫ ለመሆን የበቃችውን አዲስ አበባን "የእኛ ብቻ ናት" ብሎ መጠየቅ ከሞራል፣ ከታሪክ፣ ከህግም ሆነ ከፖለቲካ አመክንዮ አኳያ ተቀባይነት የሌለው አጀንዳ ነው። እንኳንስ ኢትዮጵያውያን እንዳንለያይ ሆነን ተቦክተን የተጋገርንባት አዲስ አበባ ከተማ፣ ራሱ ኦሮሚያ ክልልም ሆነ ሌሎች የአገሪቱ ክልሎች የሁሉም የክልሎቹ ነዋሪዎች እንጂ የአንድ ብሄር ክልልና ንብረት ብቻ ሊሆኑ አይችሉም። የአገሪቱ የምስረታ ሂደት የደረሰበት የእድገት ደረጃ ይህ እንዲሆን የማያስችል ከመሆኑም በላይ እንዲህ አይነት ሊተገበር የማይችል መብት የሚሰጥ ህግም እስካሁን በአገራችን የለም። "አለ" ከተባለም የህጎች ሁሉ የበላይ ህግ ከሆነው ከፌደራሉ ህገ-መንግስት የሚቃረን የተሳሳተ ህግ ነው የሚሆነው።

በአለፉት አምስት ዓመታት በአዲስ አበባ ጋሞዎች በማንነታቸው ተለይተው ሲገደሉ፣ የትግራይ ተወላጆች በጅምላ ከስራ ሲባረሩና ሲታሰሩ፣ አማራዎች ተለይተው ቤታቸው ሲፈርስና ወደ ከተማዋ እንዳይገቡ ሲታገዱ፣ መስጊዶችና አብያተ-ክርስቲያናት በቡል ዶዘር ሲፈርሱና በአጠቃላይም ኦሮምኛ ተናጋሪ ያልሆኑ ዜጎች ቤት ሰርተው የማይኖሩበት “ሸገር” የሚባል “ቦምቦሊኖ” መሰል አፓርታይዳዊ የከተማ ቀለበት ሊመሰረት ሲታሰብና የአዲስ አበባ ህዝብ በከበባ ውስጥ እንዲገባ ሲደረግ በገሃድ አይተናል። አሁን ደግሞ ከተማዋ ከየት ተነስታ የት እንደደረሰች የሚያሳየው ታሪካዊ አሻራዋ እንዲጠፋና የነዋሪዎቿ ማህበራዊ ትስስር እንዲበጣጠስ ሲደረግ እያየን ነው። ይህ ሁሉ እየሆነ ያለው በአስተዳደር እውቀት ማነስ ሳይሆን ይልቁንም ጠባብ ፖለቲካዊ ዓላማን ዕውን ለማድረግ ካለ ድብቅ ፍላጐት ነው።

አገዛዙ ይህንን ሁሉ እያደረገ ያለው ያለ ምክንያት አይደለም። ከፖለቲካ የኃይል አሰላለፍ አኳያ አዲስ አበባን መቆጣጠር ስላለው ስትራቴጂክ ጠቀሜታ ከተቃዋሚው ጐራና ከህዝቡ በላይ ጠንቅቆ ያወቀ በመሆኑ ነው። ድርጊቱ አንድን ከተማ በብቸኝነት በመቆጣጠር ብቻ የተወሰነ ሳይሆን የራስን አገር የመፍጠር ትልቅ ፕሮጀክት አካል ነው። ይህ በአዲስ አበባም ሆነ በአገር ደረጃ አክራሪ የኦሮሞ ብሄርተኞች እየፈጠሩት ያለው አደጋ አንድን ብሄር ለይቶ የሚጎዳ ሳይሆን የኦሮሞን ህዝብ ጨምሮ መላውን የአገሪቱን ህዝብ የሚጎዳና የአገሪቱን የመፍረስ ሂደት የበለጠ በማፋጠን አይቀሬ የሚያደርግ ነው።

ተቃዋሚዎች በ32 አመቱ የትግል ሂደት የመንግስት ወይም የስርአት  ለውጥ ማምጣታ ቢሳነን እንኳ ቢያንስ አዲስ አበባን አሸንፈን ተቆጣጥረን ቢሆን ኖሮ አሁን ላይ በምንገኝበት አደጋ ላይ ባልወደቅን ነበር። 1997 ዓ.ም “ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ” የአዲስ አበባ ምክር ቤትን ካሸነፈ በኋላ ያን በህዝብ ትግል የተገኘውን ታሪካዊና ከፍተኛ ውጤት ሜዳ ላይ ባይበትነው ኖሮ የወቅቱ የአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ በብዙ አዎንታዊ መመዘኛዎች ምን ያህል የተሻለና የተለየ በሆነ ነበር።

በአዲስ አበባ ዙሪያ እየመጣ ያለውን የአደጋ መጠን በልኩ ካልተረዳነው በስተቀር በከተማዋ ዙሪያ አዳዲስ ነገር በተፈጠረ ቁጥር እንደ አዲስ በመገናኛ ብዙሀን በመጯጯህ የምናመጣው ለውጥም ሆነ የምናስቀረው አደጋ የለም። ያለ ጥናት ህንጻና መንደርን ማፍረስ ስህተት ቢሆንም አገሩ እየፈረሰ ባለበት ወቅት ለህንጻና ለመንደር መፍረስ መጮህ እምብዛም ትርጉም የለውም።

ከ75 በመቶ በላይ የሚገመተው የአገሪቱ የፋይናንስ አቅምና የተማረ የሰው ኃይል የሚገኝባት አዲስ አበባ ከተማ የኢትዮጵያ ህዝብ ታሪካዊ ትስስርና አብሮነት ዋና እምብርትና ቋጠሮ ነች። አሁን ላይ በየክልሉ እየተካሄደ ባለው የእርስ-በርስ ጦርነት እየተፋጠነ ያለው የአገሪቱ የመፍረስ ሂደት በጠንካራ ትግል እንዲቆም ካልተደረገ በስተቀር ሄዶ ሄዶ መጨረሻ ላይ የሚቋጨው አዲስ አበባን አርማጌዶን በማድረግ ነው። ከዚህ በተፃራሪ የመፍረሱ ሂደት በትግል ሊቆምና የህልውና መድህን ሊገኝ የሚችለውም በዋናነት አዲስ አበባ ላይ ተጨባጭ ለውጥ ከመጣ ብቻ ነው።

ስለሆነም ይህ የህልውናችን የመጨረሻ ቋጠሮ እንደዋዛ ተበጣጥሶ አገሩ እንዲበተንና፣ በዚያም ምክንያት አገርና ዜግነት የለሽ መሆንን ማንም ህሊና ያለው ዜጋና ህዝብ በፀጋ ሊቀበለው አይገባም። ከስድስት

ሚሊዮን በላይ የሆነው የአዲስ አበባ ህዝብ ራሱን ችሎ ከ70 በላይ ከሚሆኑት የዓለም አገራት የተናጠል ቁጥር የበለጠ የህዝብ ብዛት ያለው በመሆኑ በአግባቡ ከነቃና ከተደራጀ ራሱን በብቃት መከላከልና ህልውናውን ማስከበር የሚችል ህዝብ ነው። ይህ አቅምና ብቃት በተገቢው ጊዜና ሁኔታ ጥቅም ላይ ካልዋለ ግን የኃይል ሚዛኑ በሂደት እንዳይመለስ ሆኖ ሊቀየር እንደሚችል መገንዘብ ይገባል።

ትግሉ ዓላማዬን በማንኛውም መንገድ (በዲሞግራፊ ለውጥ ጭምር) ማሳካት አለብኝ ብሎ ከሚያምን አጅግ አደገኛና ፅንፈኛ የሆነ ብሄርተኛ ኃይል ጋር የሚካሄድ ስለሆነ በእንዲህ ዓይነቱ ትግል ጊዜን ቀድሞ መገኘት እጅግ አስፈላጊና ምትክ-የለሽ ቁም-ነገር መሆኑን በአግባቡ መገንዘብ ያስፈልጋል። የአገዛዙ የወቅቱ አይን-አውጣ አካሄድ ከወዲሁ በትግል መገታት ካልቻለ አንድ የምርጫ ዘመን ካለፈ በኋላ ግን ሁኔታዎች እስከወዲያኛው እንዳይመለሱ ሆነው ሊለወጡ ይችላሉ። አገዛዙ ሌት ከቀን እየባዘነ ያለው ይህን አይነቱን ሁኔታ መሬት ላይ ለመፍጠር ነው።

ሰላማዊ ትግልን የመሰለ ኃያል ትጥቅ በእጁ መዳፍ ውስጥ ይዞ የሚገኘው የአዲስ አበባ ህዝብ ታጣቂ ኃይሎች ከጫካ መጥተው ነፃ እንዲያወጡት ቁጭ ብሎ መጠበቁን ማቆምና የራሱን ትግል በአስአቸኳይ ማካሄድ አለበት። "እየመጡ ነው" የሚለው ሰሞነኛ ዘፈን የራሱ መልእክት ቢኖረውም የህዝቡን ትግል የሚያዘናጋና የአገዛዙን ዕድሜ የበለጠ ለማራዘም የሚያስችል አደገኛ ምኞት ነው። የትግሉ ፋና-ወጊ መሆን የሚገባው ከተሜና አገራዊ ልሂቅ በሌሎች ትግልና መስዋዕትነት ነፃ እወጣለሁ ብሎ ሲጠብቅ ማየት ከሞራልም ሆነ ከውጤታማነት አኳያ የተሳሳተ ምርጫ ነው።

ይህ ትውልድ በታሪኩ ከዚህ ጉዳይ በላይ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ፣ በጋራ ተባብሮ ሊቆምለትና በጋራም ሊሞትለት የሚገባው ሌላ አሳሳቢ አጀንዳ በአሁኑ ወቅት ሊኖረው አይችልም። አገዛዙ ለህዝቡ ያለው ከፍተኛ ንቀት በአስቸኳይ መቆም አለበት። ሌላውን ሁሉ ትተነው ከጥቂት አመታት በፊት ከእነዚህ አክራሪ ብሄተኞች "የአዲስ አበባን ህዝብ የውሃ አቅርቦት እናቋርጣለን" የሚል ዛቻ በአደባባይና በድፍረት ሲነገር እስከ ዘር ማጥፋት የሚደርስ የህልውና አደጋ ከፊቱ እየጠበቀው እንደሆነ ህዝቡ ተገንዝቦ አደጋውን ከጅምሩ ለመቀልበስ የሚያስችል ርብርብ ማድረግ ነበረበት። "በውሀ ጥም እገድላችኋለሁ" ብሎ አንድ ጊዜ ለመዛት የደፈረ ኃይል፣ የጊዜ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር ላይፈፅመው የሚችል ምንም አይነት እኩይ ተግባር አይኖርም። ስለሆነም ጉዳዩ የመላው አገሪቱ ህዝብ የህልውና አደጋ መሆኑን በመገንዘብ "ጊዜ የለንም" በሚል ፍጥነት ሁላችንም በጋራ ቁመን አገዛዙን በድፍረትና በጽናት ልንታገለው ይገባል።

ይሁንና እንዲህ ዓይነቱ ትግል የወረቀት መግለጫ በማውጣት፣ ቁጭ ብሎ በማማረርና በማለቃቀስ፣ ውጤቱን ከሌሎች በመጠበቅና የጥቂቶችን የትግል እንቅስቃሴ ዳር ላይ ቆሞ በመታዘብ ለውጤት ሊበቃ አይችልም። እንዲህ አይነቱ አካሄድ በአገዛዙ መናቅን እንጂ ሌላ የሚያስገኘው ውጤት የለም። ህዝብን በስፋት የሚያሳትፍ፣ ተከታታይነት ያለው፣ ዋጋ ለመክፈል የተዘጋጀ፣ የተቀናጀና የተደራጀ ሠላማዊ የህዝብ ትግል በፍጥነት መጀመርና ማካሄድን ይጠይቃል። በስራ ላይ ባሉትም ሆነ አዲስ በሚፈጠሩ ፓርቲዎች ዙሪያ መደራጀትና ከ97 ዓ.ም በኋላ በተለያዩ ምክንያቶች የፖለቲካ ማዕከልነቷን ያጣችው አዲስ አበባ እንደገና ወደ ቀደመ የትግል መሪነት ሚናዋ እንድትመለስ ማድረግ ያስፈልጋል።

በአሁኑ ወቅት በህገ-ወጥ መንገድ እየተፈጸሙ ያሉ ጥቃቶችን ህጋዊ በሆነ ተከታታይ ሰላማዊ ሰልፍና ህዝባዊ እምቢተኝነት መመከት፣ መዋቅራዊ የሆኑ ችግሮችን ደግሞ በምርጫ የፖለቲካ ሂደት የጎላ የትግል ተሳትፎ በማድረግ በዘላቂነት መለወጥ ይገባል። ይህንን ማድረግም ይቻላል።

አገዛዙን በምርጫ ታግሎ ማሸነፍ ከአሁን በፊት በተግባር የፈፀምነው ጉዳይ ስለሆነ እንደማይቻል ተደርጎ መታየትና መፈራት የለበትም። አገዛዙ በዙሪያው ያሰባሰበው ኃይል በገንዘብና በስልጣን ጊዜያዊ ጥቅም እንጂ በዓላማ አንድነት የተሰባሰበ ባለመሆኑም የህዝብን ጠንካራ ህጋዊና ሰላማዊ ትግል ለሳምንታትም የመቋቋም ብቃት አይኖረውም። ችግሩ ሰላማዊ ትግል የሚባል ኃያል አቅም በእጃችን ያለ መሆኑን አለመገንዘባችን ነው።

ስለ ምርጫ ፖለቲካ ስናስብም የግድ በየአምስት ዓመቱ አንድ ጊዜ የሚመጣን አገራዊ ምርጫ መጠበቅ የለብንም። የፖለቲካ ኃይሎች ተገቢ የሃሳብ ንቃት፣ ተገቢ የትግል ትብብርና አንድነት ፈጥረን ህዝቡ በሰላማዊ ትግል አዋጪነታ ልባዊ እምነት ኖሮት በሙሉ ልብ የትግሉ ተሳታፊ እንዲሆን ማድረግ ከቻልን በእየአንዳንዱ የምርጫ ወረዳ የአስር ሺህ ነዋሪዎችን የተቃውሞ ፊርማ /Petition/ በማሰባሰብ ብቻ በአዲስ አበባ ድጋሚ ምርጫ እንዲካሄድ ማድረግ ይቻላል። ይህንንም በማድረግ ምንም ዓይነት የኃይል አማራጭን መጠቀም ሳያስፈልግ የወቅቱን የአዲስ አበባን መስተዳድር ፍጹም ሰላማዊና ህጋዊ በሆነ መንገድ በወራቶች ውስጥ በምርጫ ማሸነፍና የ1997ቱን ታሪክ መድገም ይቻላል።

ፓርቲዎች እውነተኛና ጠንካራ አማራጭ ኃይል ሆነን ከቀረብንለት አሁን ላይ የህልውና አደጋውን በግልፅ እያየው የመጣው ህዝብ ከጎናችን እንደሚቆም መጠራጠር አይገባም። ለጥቂት የስልጣን ጥመኞች ሲባል በስሙ እየተነገደበት ያለው የኦሮሞ ህዝብም በተሳሳተ ትርክት ምክንያት ያለአግባብ የጥቃት ሰለባ ሲሆኑ ከታዩት ሌሎች ህዝቦች በመማር ከሌላው ህዝብ ጋር ተባብሮ አገዛዙን ሊታገለው ይገባል።

የአዲስ አበባ ህዝብ ትግል ከራሱም አልፎ ለመላው አገሪቱ ደህንነት የሚተርፍ ሊሆን ይገባል። አዲስ አበባን አሸንፎ መረከብ አገዛዙን በአገር ደረጃ ለማሸነፍም ሆነ አገሪቷንና ህዝቧን በዘላቂነት ከህልውና ጥፋት ለመታደግ አስፈላጊ ቅድመ-ሁኔታ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። ኢዜፓ ይህንን እውነታ አስቀድሞ ስለተረዳ ነበር በ1992 ዓ.ም በተካሄደው ምርጫ "ቀዳሚ ዓላማችን አዲስ አበባን ነፃ ማውጣት ነው" የሚል መሪ መፈክር አንግቦ የተወዳደረው። በ1997 ዓ.ምህረቱ ምርጫም ጠንካራ ዝግጅት አድርጎ አብላጫውን የአዲስ አበባ ምክር ቤት መቀመጫ ለማሸነፍ የበቃው።

በሌሎች ደካማ አስተሳሰብ ምክንያት ሳይሳካለት ቢቀርም፣ ኢዜፓ በ2013 ዓ.ም በተካሄደው ምርጫም ተቃዋሚዎችን አስተባብሮ ለመወዳደር ጥረት ያደረገው ቢያንስ አዲስ አበባን ማሸነፍ እንችላለን የሚል ፅኑ እምነት ስለነበረውና ይህም ወደ ላቀ ድል የመስፈንጠሪያ አቅም እንደሚፈጥርለት በመገንዘብ ነበር። ነገር ግን አብዛኞዎቹ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ከመተባበር ይልቅ በተናጠል መሮጥን ስለመረጡ ውጤቱ ሳያምር ቀርቷል። እንዲህ አይነቱ የግለኝነት አካሄድ በወደፊቱ ትግልም ሆነ የምርጫ ሂደት የሚቀጥል ከሆነ ግን ውጤቱ ምርጫ መሸነፍንና ስልጣን ማጣትን ብቻ ሳይሆን እስከወዲያኛው የአገርና የህዝብ ህልውና ማጣትን የሚያስከትል ሊሆን ይችላል።

ከረጅም ጊዜ የትግል ልምዱ በመነሳት በእርግጠኝነት ልናገር የምችለው ተቃዋሚ ፓርቲዎች ካለፉት 32 ዓመታት በተለየ መተባበርና መደማመጥ ከቻልን፣ ከአሉባልታና ከሴራ ፖለቲካ ራሳችንን በማራቅ ፈጠራ የታከለበት አዲስ ሃሳብን ለመቀበል ከተዘጋጀን፣ በሰላማዊና ህጋዊ መንገድ ብቻ ይህንን ከህዝብ የተነጠለ ደካማ አገዛዝ ማሸነፍ እንደምንችል ጥርጥር የለኝም።

የወቅቱ ትግል ለስልጣን የበላይነት የሚካሄድ የፖለቲካ ትግል አይደለም። በህልውና ለመቀጠል የሚደረግ የሞት የሽረት ትግል ስለሆነ ለፖለቲካ ፓርቲዎች ብቻ የሚተው አይደለም። ለዛሬ ያልሆነ አገርና ህዝብ ወዳድነት ትርጉም የለሽ ነውና ተፅዕኖ ፈጣሪና ታዋቂ የሆናችሁ ምሁራን፣ የሀይማኖት አባቶች፣ ሲቪክ ማህበራት፣ ባለ ሀብቶች፣ አርቲስቶች፣ ስፖርተኞች፣ ወዘተ... የዳር ተመልካችነትን ትታችሁ የትግሉ ዋና ተዋናይ መሆን አለባችሁ። ዝና፣ ክብርም ሆነ ባለጸጋነት አገርና ህዝብ ከሌለ ትርጉም የለሽ ነውና።

አገሩ ከፈረሰ የሁላችንም ዕጣ-ፈንታ የሚሆነው በታጣቂ ሃይሎች በግፍ እየተገደሉ ማለቅ አልያም አገርን ጥሎ መሰደድ ነው። በአጠቃላይ አዲስ አበባ የመዳኛችን መጀመሪያ ወይም የመጥፊያችን መጨረሻ የመሆኗ እድል የሚወሰነው በአገዛዙ ሳይሆን በኛ ጥንካሬና ድክመት ነው። አገርና ትውልድ መቀጠል ካለበት ከዛሬ ቆጥበን የምናሳድረው ምንም ዓይነት መስዋዕትነት ሊኖር አይገባም።በእንባ ብቻ ሳይሆን በላብና በደም ጭምር ዋጋ ከፍለን ህልውናችንን ማስጠበቅ አለብን።

በእኔ በኩል እንደ አንድ የአገርና የህዝብ ህልውና የሚያስጨንቀው ዜጋና የፖለቲካ ሰው ለዚህ አይነቱ ትግል ስኬታማነት የሚጠበቅብኝን ሁሉ ዋጋ ለመክፈል ዝግጁ ነኝ። እናንተስ? መልሳችሁ አዎንታ ከሆነ መቼና እንዴት ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ መግባት እንደሚቻል በግልጽና በፍጥነት ሳይመሽብን እንወያይ፣ እንወስን፣ እንተግብር። ከዚህ በላይ ለመዘግየት የሚያስችል ጊዜ የለንም።/**ልደቱ አያሌው መጋቢት 19 2015 ዓ.ም/**

**ልደቱ አያሌው**

**መጋቢት 21 2016 ዓ.ም**